
# ናይል



Nile 7th year; publication No.3; January, 2020

ናይል 7ኛ ዓመት፣ ቁጥር 3፣ ጥር 2013 ዓ.ም

## የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስፖርት አካዳሚ የስፖርት ስልጠና ልዕቀት ማዕከል ለመሆን አቅዶ እየሠራ ይገኛል

በትዕግስት ዳዊት

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስፖርት አካዳሚ የስፖርት ስልጠና ልዕቀት ማዕከል ለመሆን አቅዶ እየሠራ ይገኛል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስፖርት አካዳሚ ከኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበር ጋር ባደረገው የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት መሰረት በርካታ ሥራዎችን አከናውኗል፡፡

በተለያዩ የስፖርት ዘርፎች ላይ ያተኮሩ አገር አቀፍ አውደ ጥናቶችንና ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ለስፖርቱ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

በዚህ ረገድ የስፖርት አካዳሚው ከኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበር እና ከኢትዮጵያ ቴንስ ፌዴሬሽን ጋር በመተባበር ከታህሳስ 13-23 2013 ዓ.ም ባሕር ዳር ያዘጋጀውንና ከሃገር ውስጥ እና ከውጭ ሃገር በመጡ ከፍተኛ ባለሙያዎች የተመራውን የአንደኛ ደረጃ የቴንስ አሰልጣኝነትና የዳኝነት ስልጠና በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ጽንሰ ሃሳብንና የተግባር ላይ ልምምድን ባማከለው በዚህ ስልጠና ከሃገሪቱ 35 ዩኒቨርሲቲዎች የተወከሉ የስፖርት ሳይንስ ምሁራን ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ ሰልጣኞቹ በአካዳሚው ቆይታቸው ስፖርቱን በዘላቂነት ለማስፋፋት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተወያይተዋል፡፡ የቴንስ ስፖርትን በማህበረሰቡ ውስጥ ለማስረጽ የሚረዱ ምክረ-ሃሳቦችንም ሰንዝረዋል፡፡




የአንደኛ ደረጃ የቴንስ አሰልጣኝነትና የዳኝነት ስልጠና ተሳታፊዎች እና አሰልጣኞች በጋራ

በስልጠናው የማጠቃለያ ፕሮግራም ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ስፖርት አካዳሚ ተወካይና የአካዳሚው የድህረ-ምረቃ፣ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ዲን ዶ/ር ተከተል

ወደ ገፅ 5 ዞሯል




በውስጥ ገፆች

3 ክፉ ቀን ጥሩ ነው
11 ፀሀይ ናፋቂዋ
7 ... የዕውቅና ሽልማት አገኘ
8 የነገውን አብሮነት...
9 ታላቅነት ማለት ምን ማለት ነው?
15 ከዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ ጋር የተደረገ ቆይታ






# ናይል

በኢንፎርሜሽን እና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት
በውስጥ ግንኙነት እና ኮሚኒኬሽን ክፍል የሚዘጋጅ ወርሀዊ ጋዜጣ

**ዋና አዘጋጅ**

ትዕግስት መኮንን

**ግራፊክስ ዲዛይነር**

ትዕግስት መኮንን

**ዘጋቢዎች**

ሙሉጎጃም አንዱዓለም
ወንዳለ ድረስ
ሙሉጌታ ዘለቀ

ትዕግስት ዳዊት

**ፎቶግራፈሮች**

ታምራት አታላይ
በሪሁን ታረቀኝ
ቤተልሄም ወርቅነህ

**አምደኞች**

ደስታ ተከስተ
ዳኘነት ደረበ
ወንድም መልካም
አቶ አብርሃም በላቸው
አቶ ተሾመ አጀበው

**አርታኢ**

አቶ ሀሰን ኡስማን

**መልእክተኛ**

መልሸው አጥናፉ

**ፀሀፊ**

መለሰው አደመ
አበባ ካሳው

**ሾፌር**

ላመስግን ጫኔ

**አባይ ማተሚያ ቤት ታተመ**
**ጥር 2013 ዓ.ም**

Contact us:-
https://www.bdu.edu.et
http://www.twitter.com/bdueduet
https://www.facebook.com/bduethiopia
http://www.linkedin.com/school/bahir-dar-university
+251583209653

# ርዕሰ-አንቀጽ

## ክፉ ቀን ጥሩ ነው!

ነፍሳቸውን በአጸደ ገነት ያኑርልንና በቅርቡ በሞት የተለዩን እውቁ የሀገራችን ምሁር ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም በበርካታ ዘመን ተሻጋሪ ስራዎቻቸው ብዙ ብለው፣ወገኖቻቸውን አስተምረው፣ መክረውና ዘክረው አልፈዋል::

ለዛሬው "አገቱኒ" በሚል ርእስ ለህትመት በበቃው መጽሀፋቸው በስፋት በዳሰሱትና ከላይ በርእስ በተመለከተው ጉዳይ ላይ ትኩረታችንን አቅንተናል።

ፕሮፌሰር መስፍን በተጠቃሹ መጽሀፋቸው አጽንኦት ሰጥተው "ክፉ ቀን ጥሩ ነው" ይሉናል። ክፉ ቀን ጥሩ ቀንን እየጮኸ እንደሚጣራም አበክረው ያስገነዝቡናል።

የመጪው ጥሩ ቀን ምልክት የሆነው ክፉ ቀን እንደተባለው በሌሊት ጨለማ ይመሰላል። የሌሊቱ ጨለማ ለእንቅልፍ እንደሚጠቅም የቀኑ ብርሀንም ለስራ ይበጃል::

ለህይወት እንቅልፍም ስራም በግድ ያስፈልጋሉ። ስለዚህም ይፈራረቃሉ። የተፈጥሮ ህግ ነውና ጨለማው በብርሀን ይወገዳል፤ ክፉ ቀንም እንዲሁ ለጥሩ ቀን ቦታውን ይለቃል። በጨለማ ህይወት ሊቀጥል እንደማይችል ሁሉ በክፉ ቀንም ህይወት አይቀጥልም።

ክፉ ቀን መታደስ ስለማይችል ይሻግታል፤ ስለሚሻግት የክፉ ቀን ብል ይበላዋል። ራሱን በራሱ ጨርሶም እንደተባለው ለጥሩ ቀን መንበሩን ያመቻቻል።

ክፉ ቀን ክፋት በጎነትን አሸንፎ እንደ ማይዘልቅ ያሳያል:: ክፉ ቀን የጠራ መስታውት ነው:: መልካችንን ብቻ ሳይሆን ባህሪያችንንም፤ ጤናችንን ብቻ ሳይሆን ህመማችንንም፤ ውበታችን ብቻ ሳይሆን አስከፊነታችንንም ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ክፉ ቀን የህዝብነትን ጥሪ እንድናዳምጥ ከራስ በላይ ነፋስ በሚል እምነት ላይ ቆመን የግል ኑሮ ማነቆን ንድንበጥስ፤እንድንተሳሰብ፤የእድገት ጉዞ እንቅፋቶችን እንድንናስወግድ ያሳስበናል። ክፉ ቀን የነጻነት ነጋሪት፣ የህጋዊ ስርአት ዋዜማ፣ የህዝብ ስልጣን ባለቤትነት መለከት ሆኖ ህዝብን ለድል አክሊል ያዘጋጃል:: ለቅዱስ መንፈስ መልእክተኞች መንገዱን ይጠርጋል።

መማር የፈለገውን ያስተምራል ደጋግ ሰዎችን ይቀሰቅሳል፣ ያስተባብራል። በተለያየ የኑሮ ደረጃ የተከፋፈሉትን በአላማ ያስተሳስራል። የግፍን መራራነትም እንዲቀንሱት ያበረታታል።

ክፉቀንያስተዛዝባል፤ትእቢተኛውንና ሀሰተኛውን ወዳጆቹ እስኪታዘቡት ያጋልጠዋል። ህሊናን በጨንራ እስከመሸፈን ያደርሳል። ለወዳጅ ባላንጋራ፣ለልጆች ማፈሪያ መሆንን ያስከትላል። ከዚያም አልፎ ብዙ ጉድ ያሳያል። ያበጠውን ያፈነዳል፤ ክብርን ወደ ውርደት ውርደትን ወደ ክብር ይለውጣል።

ያለፈውን ካለው ጋር በእውነት እንድናወዳድረው ያስገድደናል:: የእውነትንና የሀሰትን፣የዓፍንና የህጋዊ ስርአትን ድንበር ያሳየናል:: የጭካኔን ወሰን የለሽነት በግልጽ ያመላክተናል። የግፍን ጥርስ ሁሉም እንዲያየውና እንዲቀምሰው ያደርጋል። አልፎ ተርፎም ህጋዊ ስርአትን እንድንናፍቅ ምክንያት ይሆናል።

ክፉ ቀን ቀኖችን ሁሉ ሳይለያይ ዛሬ ያደርጋቸዋል። ትናንትን ወደ ዛሬ ለውጦ ነገንም ዛሬ ለማድረግ ይመኛል። ጊዜ ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ እንደማይሄድ ያሳውቀናል።

እዚህ ላይ ክፉ ቀን ተስፋ የሚያስቆርጥ ሳይሆን ተስፋን በምጥ የሚያዋድ ብስራት ሆኖ ይዘልቃል:: እንደተባለው ህይወት በምጥና በስቃይ ይጀምራል። የህይወት ጣእም ምጡንና ስቃዩን ያስረሳል።

ህይወት ህይወትን፣ፍቅርን፣ እድገትንና ተስፋን ያወርሳል፤ የእውቀት፣የጥበብና የስልጣኔ ሁሉ ምንጭ የሆነው ህይወት ፋታ የማይሰጥና የማያቋርጥ የተከታታይ ትውልዶች ጉዞ እንደሆነ ይታወቃል:: በዚህ ጉዞ እጅ ለእጅ ካልተያያዙ በየመታጠፊያውና በየገደላ ገደሉ የመለያየት አደጋ ይገጥማል:: ይህን ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተስተዋሉት የሀገራችን ታሪካዊ ክስተቶች ተመልክተናል።

እናም ለጉዳዩ የምንሰጠው ተገቢ ትኩረት የዘመናትን ድንበር በጽናት ለመሻገር ብሎም ሀገራዊ አንድነታችንንና የቆየ አብሮነታችንን በዘላቂነት ለማስቀጠል የሚያስችለን እንደሚሆን ይታመናል።




## ፀሀይ ናፋቂዋ ከገፅ 12 የቀጠለ

ግን እድሜ ከመቁጠር እና የሰውነት መጠን ከመጨመር ውጭ ቆሞ መሄድ የማይታሰብ ነገር ሆነ።

አባቴም ከእናቴ በኂላ ካገባት ሚስቱ ስለወለደ ለእኔ ምንም ቦታ አይሰጠኝም አልፎ አልፎ ለእናቴ ትንሽም ቢሆን ብር በሰው ይልክላታል።አንዳንድ የእናቴ የቅርብ ጓደኞችም ሁኔታዋ ስላሳዘናቸው በሚችሉት ሁሉ ነገር ይረዷት ጀመር።

ሦስት አመት ከሞላኝ በኂላ እናቴ ተስፋ ቆርጣ በየቦታው ይዛኝ መሄዱን በማቆም የዘወትር ስራዋን ቀጠለች:: ስራዋን በምትሰራበት ጊዜ ከገመድ ከተሰራች አጭር ኩርሲ ላይ ቁራጭ ልብስ በማድረግ ታስቀምጠኛለች:: በእግሬ ቁሜ መንቀሳቀስ እና ቀኝ እጄን እንደፈለግሁ ማዘዝ አልችልም ፤የመቀመጥ ችግር ግን የለብኝም፤በምናገርበት ጊዜም ምላሴን የተወሰነ ይይዘኛል፣ጥርት ያለ አማርኛ መናገር አልችልም።

እናቴ ታግዘኛለች ብላ የቀጠረቻት ልጅም በቃኝ ብላ ሄደች። ምን ታድርግ ከቦታ ቦታ የማትንቀሳቀስ፣ የማትስቅ፣የማትቦርቅ፣ከኩርሲ ላይ ቁጭ ብላ የከንፈር መምጠጫ የሆነች ልጅ መያዝ ሰለቻት።እናቴ ከዚያን ቀን በኂላ ገብያም ሆነ ሌላ ቦታ ለመሄድ በጣም ተቸገረች።

እኔንም ሆነ እርሷን ለማስተዳደር የግድ መስራት አለባት፤ እናም ከኩርሲዋ ላይ እንደተቀመጥሁ ጎረቤት ተመላከቷት ብላ ትታኝ ትሄዳለች።

በዚህ ሁኔታ እንዳለን አምስት አመት ሞላኝ።ከሰውነቴ መጨመር በስተቀር ምንም የተቀየረ ነገር የለም።ነገር ግን በህይወታችን ውስጥ አዲስ ነገር ተከሰተ።

ይቀጥላል....

ቀጣዩን ክፍል በሚቀጥለው ዕትም ይጠብቁ!

# ሠሞነኛ

ይህ አምድ ከዜናዎች በተጨማሪ ወቅታዊ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ ሀተታዊ ፅሁፎች ይቀርብበታል

## ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የገና ሰሞን

### "ባሕር ዳር እንደቤቴ"



የ2013ዓ.ም የገና በዓልን በጋራ ለማድረግ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ "ባሕር ዳር እንደቤቴ" በሚል ስያሜ ተማሪዎች አመት በዓል ሲያከብሩ እንደቤታቸው እንዲሰማቸው ለማድረግ በከተማው የሚገኙ ፈቃደኛ ወላጆች ጋር እንዲያከብሩ ተማሪዎችን ባላደራ ወላጆች ጋር ሲያገናኙ።



በዘንድሮው የገና በዓል በከተማው ከሚገኙ ባላደራ ወላጆች ጋር በዓሉን አብረው ካከበሩ 400 የሚሆኑ ተማሪዎች በተጨማሪ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ እና የባሕር ዳር ወጣቶች አጋር አካላትን በማስተባበር ሌሎች ከሶስት መቶ በላይ የሆኑ ተማሪዎችን በድብ አንበሳ ሆቴል በ ማዕድ ማጋራት ተችሏል።



"ምክኒያታዊና ንፁህ ትውልድ እንፍጠር" በሚል በተመራቂ ተማሪዎች የተቋቋመው ማህበር የከተማውንና የፔዳ ግቢ ማህበረሰብን በማስተባበር የ2013 ዓ.ም የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ በዕለቱ ወደ 500 የሚጠጉ አቅመ ደካሞችን ሲመግቡ።






## የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች ድጋፍ አደረገ



የባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ አመራሮች የተለያዩ የዕርዳታ ቁሳቁሶችን ለክልሉ ምግብ ዋስትና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር ወ/ሮ እታገኘሁ አደመ ሲያስረክቡ



በትዕግስት ዳዊት

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንፎርሜሽን እና ስትራቴጅክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕ ዶ/ር ዘውዱ እምሩ ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ጊዜያት በተለያየ ምክንያት ለተፈናቀሉ እና እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው አካላት የተለያዩ ድጋፎችን ሲያደርግ መቆየቱን ተናግረው ዛሬ በቤኒሻንጉል ክልል በተለያዩ ዞኖች ተፈናቅለው በየመጠለያ ካምፖች ለተጠለሉ ተፈናቃዮች የሚውል የምግብ የአልባሳት እንዲሁም የተለያዩ የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ማበርከቱን ተናግረዋል፡፡

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የግብርና እና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ በምርምር ያገኘውን 660 ኩንታል የተፈለፈለ የበቆሎ ምርት ምንም ሳያስቀር በመተከል ዞን ለተፈናቀሉ እና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲደርስ ለአማራ ክልል ምግብ ዋስትና ኮሚሽን አስረክቧል፡፡ እርዳታውን የተረከቡት የክልሉ ምግብ ዋስትና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር ወ/ሮ እታገኘሁ አደመ እርዳታውን ሲቀበሉ እንዳሉት ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ጊዜያት እያደረጋቸው ላለው ተግባራት አመስግነው የተፈናቃዩች ችግሮች ለመርዳት መረባረብ የሁላችንም ሀላፊነት መሆኑን አሳስበዋል፡፡

ወ/ሮ ታገኝ አክለውም ለተፈናቃየች የተደረገውን እርዳታ በዩኒቨርሲቲው ስም ለተጎዱ ወገኖች እንደሚደርስ ተናግረዋል፡፡ ወደፊትም ተጎጂወች ወደ ቀያቸው እስኪመለሱ እና እራሳቸውን እስኪችሉ ድረስ መስሪያ ቤቱ እንደሚሰራ ተናግረው ልክ እንደ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ሁሉ ሌሎችም ዩኒቨርሲቲወች እና ሴክተር መስሪያ ቤቶች የየራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ዘይት 3300 ሊትር፣ ፓስታ 30 ኩንታል፣ ክክ ምስር 29.5 ኩንታል፣ ሻይ ቅጠል 500 ፓኬት፣ ሩዝ 17 ኩንታል፣ ቀይ ሽንኩርት 645 ኪ.ግ፣ የዳቦ እርሾ 1240 ፓኬት

የመመገቢያ ትሪ ብዛት 2000 ፣ማይካ የሻይ ኩባያ ብዛት 4000፣ የፕላስቲክ የሻይ ኩባያ ብዛት 650፣ ብረት ድስት ባለ 200 ሊትር ብዛት 3፣ ፍራሽ በቁጥር 300 ለተፈናቀቃዮች እንዲደርስ አበርክቷል፡፡

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በመተከል ለተፈናቀሉትና በሰላም ማስከበሩ ተግባር ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖቻችን ከዚህ በፊት ሲያደርግ ከነበረው ድጋፍ በተጨማሪ በዛሬው ዕለት አጋርነቱን በማሳየት 4.4 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ድጋፍ አድርጓል፡፡

ለምግብ ግብዓት የሚሆን የተደረገ ድጋፍ በገንዘብ ሲተመን 2,050,350 ብር፣ አልባሳትና የንፅህና መጠበቂያ እንዲሁም ሌሎች ቁሳቁሶች በገንዘብ ሲተመኑ 2,389,700 ብር በድምሩ 4,440,050 ብር የሚገመት ድጋፍ በክልሉ አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም እና ልዩ ድጋፍ የሚሹ አካባቢዎች ማስተባበሪያ ኮሚሽን በኩል ዩኒቨርሲቲው አስተላልፏል፡፡

ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ወደ ፊትም ተከታታይ እርዳታወችን እና ድጋፎችን ለተጎጂወች እንደሚያደርግ በመርሃግብሩ ላይ ተነግሯል፡፡

# የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስፖርት አካዳሚ... ከገፅ 1 የቀጠለ

አብርሃም የስፖርት አካዳሚውን የሥፖርት ስልጠና ልዕቀት ማዕከል ለማድረግ በተያዘው ተቋማዊ ዕቅድ በርካታ ተግባራት መከናዎናቸውን ጠቅሰዋል፡፡ በቀጣይ ለተቋማዊው ተልዕኮ ስኬት ሁሉም የድርሻቸውን እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል:: የስልጠናው ተሳታፊዎች በቆይታቸው የቀሰሙት ዕውቀት በሃገር አቀፍ የቴንስ ስፖርት ዕድገት የሚኖረውን ድርሻ በወጉ ተገንዝበው ለተፈጻሚነቱ በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል ብለዋል፡፡ የስፖርቱ አይነት ከዩኒቨርሲቲዎች አልፎ በህብረተሰቡ ውስጥ ተለምዷዊ እንዲሆንም የመሪ አስተባባሪነት ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ አሳስበዋል፡፡ በዶ/ር ተከተል ማብራሪያ እንደተመለከተው ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስፖርት አካዳሚ 5 የስፖርት ሳይንስ ባለሙያዎች በስልጠና ተሳታፊዎች ሆነዋል:: ሰልጣኞቹ በቀጣይ የአፈጻጸም ዕቅዶችን በመንደፍ እያንዳንዳቸው ቢያንስ 8 ወንድና ሴት ታዳጊ ስፖርተኞችን የማሰልጠን ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡

የተቋሙ የእግር ኳስ ባለሙያዎች 60 ወንዶችና 60 ሴቶችን፣ የአትሌቲክስ ባለሙያዎች በተመሳሳይ 60 ታዳጊዎችን፣ የእጅ ኳስ ባለሙያዎች ደግሞ 40 ወጣቶችን በፕሮጀክቶቻቸው አቅፈው የስፖርት አካዳሚውን ዕቅድ ለማሳካት ወደ ተግባር ገብተዋል፡፡

የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በዓል ይሆን ዘንድም የአካዳሚው ባለሙያዎች በስፋት ተንቀሳቅሰዋ፡፡

መሰረታዊ የአሰልጠኝነትና የዳኝነት ህግጋት በተወሰነ ደረጃ ለሰልጣኞች በማስጨበጥ የተማሪዎቻቸውን የቴንስ ስፖርት እውቀት ለማጎልበት ታስቦ የተዘጋጀው የባለሙያዎች ስልጠና በአሰልጣኝነትና በዳኝነት ስራ በዘርፉ የሚስተዋለውን አገራዊ የሙያ ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል መሆኑ በመዝጊያ ስነ-ስርዓቱ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የኢትዮጵያ ቴንስ ፌዴሬሽን ከፍተኛ የቴክኒክ ባለሙያ አቶ ፈይሳ ከበደ ተናግረዋል፡፡ የቴንስ ስፖርትን በተመረጡ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ማስተዋወቅ፣የተማሪዎችን ተሳትፎ ማጠናከር፣ ብሎም የዘርፉን ህዝባዊ መሠረት ማጽናት ከሠልጣኞች እንደሚጠበቅ የኢትዮጵያ ቴንስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳን አቶ ታምራት በቀለ ተናግረዋል፡፡

በማጠቃለያ ዝግጅቱ ላይ ታዳሚ የነበሩት የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ አባይ በላይሁን በበኩላቸው ስልጠናው በአሁኑ ወቅት የተቀዛቀዘውን የዩኒቨርሲቲዎች ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ይበልጥ የሚያነቃቃ እንደሚሆን እምነታቸውን ገልጸዋል::

ፕሬዚዳንቱ ወቅታዊውን የሃገራችን የሰላምና ፀጥታ ስጋት ተጋፍጠው ወደ ስልጠና ማዕከሉ የዘለቁትንና በሂደቱ የተሳተፉትን ሁሉ አመስግነዋል፡፡

በተጨማሪም ለዘርፉ እድገት መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጡ ሃገራቸውን የሚያስተዋውቁና በበጎ የሚያስጠሩ ብሎም እራሳቸውንና ሃገራቸውን የሚጠቅሙ የቴንስ ስፖርተኞችን ማፍራት በዋናነት ከስልጠናው ተሳታፊዎች እንደሚጠበቅ አሳስበዋል፡፡



ሰልጣኞች በግራውንድ ቴንስ ልምምድ ላይ

በመርሃ-ግብሩ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው ዩኒቨርሲቲውን በመወከል ተገኝተዋል፡፡ ስልጠናው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት በአጽንኦት ገልጸዋል፡፡ ሰልጣኞችና አሰልጣኞች ወደ ፊት በሚፈጥሩት የግንኙነት አግባብ ስፖርቱ የሚደርስበትን የዕድገት ሂደት መገምገም እንደሚኖርባቸው አስገንዝበዋል፡፡

የዘርፉ ባለሙያዎች የጋራ ጥረት የቴንስ ስፖርትን በማህበረሰቡ ውስጥ ለማስረጽ የሚረዳ መሆን ይኖርበታል ብለዋል፡፡

ከጀርመን ሃገር በራሳቸው ወጭ መጥተው ስልጠና የሠጡትን ኢንተርናሽናል አሰልጣኝ ዮሀንስ ወርቁን ዶ/ር ተስፋዬ አመስግነው በውጭ ሃገር የሚኖሩ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን የርሳቸውን አርአያ እንዲከተሉም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በአለም አቀፍ ደረጃ የቴንስ ስፖርት አሰልጣኝ የሆኑት አቶ ዮሀንስ ወርቁ በበኩላቸው የኢትዮጵያ ቴንስ ፌዴሬሽንን አመስግነዋል፡፡ በሁለንተናዊ መልኩ የተደራጀውን የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስፖርት አካዳሚ እና ለስልጠና የተደረገውን ከፍተኛ ዝግጅት አድንቀዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ አይነት የተሟላ የቴንስ ሜዳና ቁሳቁስ ይኖራል ብለው እንዳልገመቱ የተናገሩት አቶ ዮሀንስ ወደፊት ተጫዋቾችን ከውጭ ሃገር በማምጣት በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሜዳ እንዲለማመዱና እንዲወዳደሩ ለማድረግ ማሰባቸውን ገልጸዋል፡፡ በዚህም የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ የማፍራት አቅም የማጎልበትና የቴንስ ስፖርትን ሀገራዊ መሠረት ለማጽናት እንደሚቻል አመልክተው በሚኖሩበት ጀርመን ሃገር ሆነው ስፖርቱን በሁሉ መስክ ለመደገፍ ዝግጁነታቸውን አረጋግጠዋል፡፡

በፕሮግራሙ የማጠቃለያ ስነ-ስርዓት የአማራ ክልል ቴንስ ፌዴሬሽን፣ የኢትዮጵያ ቴንስ ፌዴሬሽንና የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስፖርት አካዳሚ የስፖርቱን ዘርፍ ለማሳደግና በጋራ ለመስራት የሚያስችል የሶስትዮሽ የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ተፈራርመዋል፡፡

ለአቶ ዮሀንስ ወርቁ ከኢትዮጵያ ቴንስ ፌዴሬሽን የማበረታቻ ልዩ ስጦታ ተበርክቷል:: ለሰልጣኞቹም እንዲሁ የተሳትፎ የምስክርነት ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

# ከዶ/ር ዳኛቸው ጋር የተደረገ ቆይታ ከገፅ 6 የቀጠለ

**ናይል፡-** አሁን ባለው የእኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ዩኒቨርሲቲዎችን እንደ ተቋም በገለልተኛነት የነፃ ሀሳብ መፍለቂያ እና ትክክለኛ የመርጃ ምንጭ ሆነው የማገልገላቸውን ጉዳይ እንዴት ይገልፁታል?

**ዶ/ር ዳኛቸው፡-** አክቲቪስቶች ዘመናቸው ነው በጊዜው የፈለጉትን ይጽፋሉ፤ ሀላፊነት የላቸውም፡፡ ምሁራኑም ይፈሯቸዋል፡፡ በተለይ የፖለቲካ ምሁሩ ይፈሯቸዋል፡፡

ገንዘብ ጉቦ ሁሉ ይሰጧቸዋል፡፡ እና በራስ መተማመን ይጎድላቸዋል:: እኔ ምሁር ነኝ ካለ አንድ ሰው በአንድ በኩል ለእውነት ተጠሪ ነኝ የሚለው ነገር በጣም ወሳኝ ስለሆነ ነው፡፡

በተለየ አደረጃጀት ላይ ስንሳተፍም በእውቀታችን፣ማህበረሰባችንን በቅንነትና በታማኝነት ማገልገል አለብን፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ መጀመሪያ ምሁሩ ራሱ ራሱን ነጻ ማውጣት አለበት፡፡ ይህንንም በግልጽ መቀበል ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ሀሳብ በተለያዩ ቦታዎች ተናግሬዋለሁ፡፡ ይህ ነገር በጣም በቶሎ መስተካከል አለበት እንጂ የባለስልጣን ልሳን መሆን የለበትም፡፡ ምሁራን ለፓርቲ ወይም ለመንግስት ተለጣፊ መሆን የለባቸውም፡፡ አንዱ ለአንደኛው መስታዉት መሆን ይገባቸዋል፡፡ ይህ የኔ አስተሳሰብ ነው፡፡ ድብብቆሽም አለ፤ ይህ መቅረት አለበት ብየ አስባለሁ፡፡

**ናይል፡-** የምሁራንም ሆነ የዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር ጥቂት በነበረበት ጊዜ፣ መንግስታትም በአንጻራዊነት አንዳንዴም ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ አምባገነን እያሉ ዘመን ተሻጋሪ እና ለዚህ ትውልድ በአርያነት የሚገለጹ በተቋማቸው እና በሀገራቸው ተጠቃሽ የሆኑ አሉ፡፡ እንዴት ይህ ሊሆን ቻለ? ከእናንተስ ምን እንማር?

**ዶ/ር ዳኛቸው፡-** ጥሩ ጥያቄ ነው ያነሳሽው፤ እኔ አሁን ትንሽ ስለ አዲስ አበባ ጥናት ሳደርግ ወደኋላ ሄደው ምህንድስና ተምረው አዲስ አበባ መዘጋጃ ቤት የተቀጠሩ ሰዎች የጻፏቸውን ብታይ ጉድ ነው የምትይው፡፡ ምህንድስና መማር ብቻ አይደለም በተባጭ የሰሯቸው ስራዎች ከተቋም ጋር የተያያዘ ነው::

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሲቋቋም በታሪክ ትምህርት ክፍል የነበሩ መምህራን የሶስተኛ ዲግሪያቸውን ተምረው መጥተው ከተቋሙ ጋር በተያያዘ የሰሩት ስራ አስደናቂ ነው፡፡ ትናንት ፕ/ር ሹመት ሲሻኝ ሲነግረኝ ነበር፡፡ ተከፋፍለው እከሌ(Midevel History) ታጠናለህ፤ አንተ Modern History ታጠናለህ ተባብለው ከተቋም ጋር የተያያዘ ውጤት ያለው ስራ ሰርተዋል፡፡ አሁን ብዙም ከተቋም ጋር የተያያዘ ስራ እየተሰራ አይደለም የምሁራን ኃላፊነትና በተቋማቸው ውስጥ የሚሰጧቸው የሥራ ድርሻ ሊፈተሽ ይገባል እላለሁ፡፡ ከተቋም አንጻር ካየነው ከድሮው ጋር ሲነፃፀር በጣም ይራራቃል፡፡

ናይል፡- ማህበረሰቡም ሆነ መንግስት እነዚህን "ምሁራን" ሊጠቀምባቸው የሚገባው በተቋማቸው ውስጥ ባላቸው ስኬት ወይም ልኬታስ መሆን አይገባም ወይ?

ዶ/ር ዳኛቸው፡- ቅድም ለማንሳት እንደሞከርኩት ምሁሩም ሆነ ማንኛውም ፓለቲከኛ እንደ ፈለገ ባርኔጣውን የሚለዋውጠው እንደ ህዝብ "Short Memory" ስላለን ነው፡፡ አሁን አሁን በመገናኛ ብዙሀን እየወጡ የሚናገሩ ሰዎች በተለያየ ጊዜ የሚቃረን ነገር ሲናገሩ ይደመጣል፡፡ ፈረንጅ ሀገር ቢሆን እንደዚህ ሲደረግ ይጠየቃል::

የዛሬ ስንት አመት እንደዚህ አላልክም ወይ? ምን ነበር ያልከው? ተብሎ ይጠየቃል፡፡ እዚህ ምንም አይደረግም፡፡ እና ለነዚህም የተመቼ ፊልድ /መስክ/ ነው የሆነው፡፡ ስለዚህ ምሁሩ ምንም የሚያደረገው የለምና ሲፈልግ የገዳም ባትሃዊ ይሆናል:: ሲፈልግ ደግሞ የናይት ክለብ አስተዳደሪ ይሆናል ሆኖ ቢቀርም የሚጠይቀው የለም፡፡ የናንተ ወጣት ጋዜጠኞች ስራ ይህ መሆን አለበት፡፡

ለዚህ ደግሞ የጋዜጠኝነት ሙያ ማደግ አለበት፡፡

**ናይል፡-** በሙሁራንና ተቋማት ግንኙነት ዙሪያ ተቋማትስ ራሳቸው ተግዳሮት አይሆኑም ትላለህ?

**ዶ/ር ዳኛቸው፡-** በሀገራችን ሁኔታዎች በጣም አስቸጋሪ በነበሩበት ጊዜም ቢሆን ትላልቅ ምሁራን ወጥተዋል::

የግድ ለሁሉም አልጋ በአልጋ የሚሆንበት ጊዜ ላይኖር ይችላል፡፡ ግን… 'You know'… ከምናሳብብ ፊት ለፊት መጋፈጥ ይሻላል:: ለምሳሌ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ነጻነት ጉዳይ በግልጽ የሀሳብ መዋጮ አድርገናል፡፡

ፈላስፋ ከ 50 አመት በፊት 'Ideals of the University' ላይ ምን ይላል መሰለሽ? ዩኒቨርሲቲ 'Chastity' ትጠብቅ፤ ከመጣው መንግስት ጋር እንደ ጋለሞታ መተኛት የለባትም ይላ፡፡ እኛ እኮ ከመጡት ጋር ነው የምንተኛው::

> "የሀሳብ ጠባቂ ነን እንላለን ነገር ግን በገንዘብ እንገዛለን ፣ ለገንዘብ እንወድቃለን::
> ለነገሩ እኛ የሀገሪቱ ሀሳብ ጠባቂ ነው የተባልነው?
> ይሆናል እንጃ?"

ይህ የተቋም ሉአላዊነት ጉዳይ ነው:: ተቋማት ውስጥ ያሉ ምሁራን ለተቋማቸው የሚመጥነውን መርመረው፣ፈትሸው መያዝ እና ለዚህ መርህ መቆም ይኖርባቸዋል፡፡ ከመንግስት ግንኙነት፣ በሙያ ነጻነት ዙሪያ ተገቢ ምክንያታዊ ውይይት በተከታታይ ሊደረግ ይገባል፡፡ ሁሉም ወጥቶ የህብረተሰብ አንቂ ወይም ተሚጋች መሆን ባይጠበቅበትም በማስተማሩ እና ምርምሩ በአግባቡ መሳተፍ በቂ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ተመሳሳይ ፍላጎት ላይኖረው ይችላል፡፡ ነገር ግን የተወሰነውን እንደ ለፍላፊ መቁጠር እና ምሁሩ የራሱን ኃላፊነት እና ስንፍና በሌላ የሚያሳብበው ነገር ጥሩ አይደለም፡፡ እኔ እንደዛ ነው ያየሁት፡፡

**ናይል፡-** ተግዳሮቶችን ተቋቁሞ ወደ ፊት ለመጓዝ ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

ዶ/ር ዳኛቸው፡- ትምህርት ላይ 'Serious' መሆን ያስፈልጋል:: ዩኒቨርሲቲዎች ወደ ቀልባቸው ለመመለስ የራሳቸውን እቅድ አውጥተው አንድ መንፈስ ይዘው መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡ በመንግስት እና በዩኒቨርሲቲ መካከል ያለው ግንኙነት ከሚያስፈልገው በላይ መሆን የለበትም፡፡ የጀርመኑ

ዩኒቨርሲቲ የራሷ መንፈስ ያስፈልጋታል፡፡ ያንን አንድ መስመር ማለፍ የለባትም፤ ግን ይሄ ማለት አይ እኔ አትድረሱብኝ ሊባል አይችልም፡፡ ገዳሞ አይደለም ዩኒቨርሲቲ፡፡

**ናይል፡-** ከተቋም አንጻር ስለ ምሁራን ሚና እንዲሁም ስለ አጠቃላዩ የውይይታችን ሂደት ለአንባቢያን በቅኔ ወይም በመሰለህ መንገድ እንደመውጫ አንድ ሃሳብ ጣል ብታደርግልን?

**ዶ/ር ዳኛቸው፡-** ምሁራንን በሚመለከት ትዝ የሚለኝ ….. "የገንዘብ ያዥ ነገር በጣም ያስገርማል፤ በገንዘብ ተገዝቶ ገንዘብ ይጠይቃል፡፡"

_አለማየሁሞገስ፣'መልካ ኢትዮጵያ'_

የሀገሪቱ የሀሳብ ጠባቂ ነን እንላለን ነገር ግን በገንዘብ እንገዛለን፣ለገንዘብ እንወድቃለን፡፡ ለነገሩ እኛ ሀሳብ ጠባቂ ነው የተባልነው? ይሆናል እንጃ?

**ናይል፡-** ዶ/ር ዳኛቸው በተጣበበ ጊዜም ቢሆን ውድ ጊዜህን ሰውተህ ከኛ ጋር ቆይታ ስላደረክ በዩኒቨርሲቲውና በአንባቢያን ስም ከልብ እናመሰግናለን፡፡

# እጅ ከምን

በዚህ አምድ የዩኒቨርሲቲው ባልደረቦች እጅ ከምን ስንል አለን የምትሉት ለአንባቢ የሚበቃ ፅሁፍ ይስተናገድበታል

## የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስታይል እና ፋሽን ቴክኖሎጂ ተቋም የዕውቅና ሽልማት አገኘ







በሙሉጉጃም አንዱዓለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ተቋም ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በማከናወኑ በአገር አቀፍ ደረጃ የዕውቅና ሽልማት ማግኘቱ ይፋ ሆኗል፡፡ ሽልማቱን ምክንያት በማድረግ የተቋሙን ኢንዱስትሪ ጥምረትና ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ቢኒያም ሰለሞን ተቋሙ ባከናወናቸው ስራዎች ዙሪያ አጠር ያለ ማብራሪያ ሰጥተውናል፡፡

የአፍሪካ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ተቋም በየአመቱ የሚያዘጋጀው የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ተሳታፊ በነበሩበት በሀዋሳ ከተማ ለአስራ አራተኛ (14) ጊዜ በተካደው ፎረም የተሳተፈው የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ተቋም በሌዘር ዘርፍ በቀዳሚነት ትኩረት በመስጠት በስልጠና በምርምርና ከተለያዩ የአፍሪካና የውጭ ሀገራት ጋር በተደረገ የልምድ ልውውጥ ከአፍሪካ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ተቋም በጋራ በመሆን ላበረከተው ከፍተኛ አስተዋጾ የዕውቅና ሽልማት ማግኘቱን ነግረውናል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ተቋም አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን አቅም ለመገንባት በርካታ የስልጠና፣ የማማከር እና የምርምር ስራዎችን በመስራት እያገዘ እንደሚገኛ እና ለወደፊት በሀገሪቱ ያለውን የጥራትና የዲዛይን ችግሮችን ለመፍታት በመስራት ላይ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በተጨማሪም ከስልጠናና ከምርምር በዘለለ ተቋሙ ከኢንተርናሽናል ትሬድ ሴንተር ጋር እየሰራ ያለውን ፕሮጀክት በማጠናከር ከ50 በላይ ለሚሆኑ ስራ-አጥ ሰራተኞች ስራ መፍጠር መቻሉን፣ ሙያዊና የስልጠና ድጋፍ እያተደረገ መሆኑን፣ ከ made in Ethiopia ድርጅት ጋር በመተባበር ሀገር አቀፍ ኤግዚቢሽን ማቅረቡን፣ከኢንተርናሽናል ትሬድ ሴንተር እና "ላክሲሚ" ከሚባል ድርጅቶች ጋር በተደረገ ግንኙነት ወደ 3 ሚሊዮን ብር ገደማ የሚያወጣ ለማስተማሪያ እና ለማምረት የሚያስችል የሽመና ማሽን በነጻ ለተቋሙ ማስገኘት እንደቻሉ አቶ ሰለሞን ገልፀዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ለቆዳ ምርት ሁደት እና ውጤት የስራ ክፍል የተሰጠው ትኩርት በጣም የሚመስገን እና የሚበረታታ መሆኑን አውስተው በክፍሉ ያለው የላበራቶሪ ማሽነሪዎች እጥረት ቢቀረፍ የበለጠ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡

አቶ ቢኒያም ለሽልማቱ መገኘት አስተዋፆ ያበረከቱትን መምህራን እና የተቋሙ ሰራተኞች አመስግነዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ተቋም



# ባህረ_ሃሳብ

ይህ አምድ የተለያዩ የሀሳብ ልዩነቶችን የሚያንፀባርቁ ፅሁፎች፣ ትዝብቶች እና ክርክሮች ይቀርብበታል

## የነገውን አብሮነት በዛሬ ላይ ለማፅናት

በደስታ ተከስተ
ባ/ዳር ዩኒቨርስቲ ICT ክፍል

'ሰዉ የዘራዉን ያንኑ ያጭዳልና' ይላል ታላቁ የክርስቲያኖች መፅሀፍ፣. ገበሬ መሬቱን አርሶና አለስልሶ በፈጣሪዉ ታምኖ ነገን ተስፋ አድርጎ በማሳዉ ላይ በሚበትነዉ ዘር ዉስጥ አሻግሮ ቡቃያዉን፤ያዘረዘረ ሰብልና የአጨዳ ግዜን እያሰበ ነዉ ለዚህም ነዉ አርሶ አደር ለዘር ትልቅ ግምት የሚሰጠዉ.. ዘር ማለት የነገ ህይወትን የሚያስቀጥል ነዉ:: ማንኛችንም ብንሆን በየዕለት ኑሯችን ለነገ የሚሆን ዘር እየዘራን ህይወትን እናስቀጥላለን፤ተፈጥሮም እንዲሁ በተመሳሳይ የመዝራትና የማጨድን ህግ ትከተላለች።

የዛሬ አስተሳሰባችንና ተግባራችን የነገ እጣፈንታችንን በአብዛኛዉ ይወስናል። አሁን ላይ መልካም ነገር ብናስብና ብንከዉን ነጋችን በጎ ሁኔታ ይዞ እደሚጠብቀን ልንጠራጠር አይገባም። በአንፃሩ ዛሬ ላይ በእኩይ ምግባር ተሰማርተን ከሆነ ዉሎ አድሮ ፍሬዉን እራሳችኑ መሰብሰባችን አይቀር። ነገን የሚያኖረን የዛሬዉ ገፅታችን መሆኑን አንዘንጋ። "ፅድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም፤ ከክፉት ደግነት ሳይሻል አይቀርም::" ሲባል እንሰማለን አብዛኞቻችን እንደየ ሀይማኖታችን በፈጣሪ ዘንድ ፅድቅና ኩነኔ መኖሩን እናምናለን። ጽድቅንም ስለምንመርጥ እምነታችን የሚያዘንን እንፈፅማለን፣ እንደ እዉነቱ ከሆነ የሰዉ ልጅ ከመነሻው ለክፉ ነገር አልተፈጠረም። የተፈጠርነው በጎ የሆነ ዘር ዘርተን ለማለፍ እደሆነ ይሰማኛል።

በቅናትና ምቀኝነት ተመርተው የተንኮል ተግባር የሚፈፅሙት ሰዎች መጨረሻቸው በቆፈሩት ጉድጓድ መሆኑን ከዕየለት ገጠመኞቻችን መረዳት ችለናል። የእነዚህ ሰዎች ክፉ ስራ በነእርሱ ብቻ የሚያበቃ አለመሆኑንና ተከታዩን ትውልድ ጭምር ዋጋ እንደሚያስከፍል ተገንዝበናል። አንዳንዶች እማኝ በሌለበት በስዉር የሚከዉኑት ክፉ ምግባር ለግዜዉ የተሳካላቸዉና ደስ የሚየሰኝ ቢመስላቸዉም የተደበቀዉ ነዉራቸዉ በፈጣሪ ዘንድ ሃጢአት በመሆኑ ዋጋቸዉን በአደባባይ ሲቀበሉ ይታያሉ።

በአንድ ዘመን ላይ የእስራኤል ሕዝብ መሪ የነበረዉ ንጉሥ ዳዊት በድብቅ ክፉ ሴራ መሥራቱን መፅሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ታሪኩ እንደዚህ ነዉ፤ አንድ ዕለት ንጉሡ በሰገነቱ ላይ ሲንጎራደድ ድንገት አንዲት ሴት ወይዘሮ ገላዋን ስትታጠብ ይመለከታል። በዚህ ጊዜ ታዲያ የወንድነት ስሜቱ ይነቃቃና ፍቅር መስራት ይከጅለዋል። ንጉሥ ስለሆነ ያሻዉን ማድረግ ስለሚችል ሴትዮዋን አስጥርቶ ይተኛታል፤ ዉሎ አድሮ ያች ሴት ከንጉሡ ትፀንሳለች፤ ሴቲቱ ኦርዮን የሚባል የአንድ ምስኪን ወታደር ሚስት ነበረች ኦርዮን በወቅቱ ሀገራዊ ግዳጁን እየተወጣ በጦር ግንባር ላይ ነበር::

ንጉሥ ዳዊት የሰዉ ሚስት ማስረገዙ እንዳይታወቅበት ነዉሩን ለመሸፈን ሴራ ጠነሰሰ:: ኦርዮንም ከጦር ግንባር ተጠርቶ እንዲመጣና ከሚስቱ ጋር ተኝቶ እንዲያድርና ሚስቱም ከባሏ እዳረገዘች ለማስመሰል የታቀደዉ

**"ነገን የሚያኖረን የዛሬዉ ገፅታችን መሆኑን አንዘንጋ::"**

ሃሳብ ሳይሳካ ይቀራል:: ወታደሩ የእስራኤል ህዝብ በጠላት ተደፍሮ የጦር አለቆቼና ጓደኞቼ በዉጊያ እየተዋደቁ እኔ እቤት ገብቼ ከሚስቴ ጋር ልተኛ አልችልም ሲል አሻፈረኝ ይላል:: በዚህ ያልተሳካለት ንጉሥ ዳዊት ሌላ ተንኮል ጠንስሶ ኦርዮን ወደ ጦር ሜዳ ተመልሶ እንዲሄድና በዚያዉ እንዲሞት አደረገዉ። ንጉሡ ይህን በመፈፀሙ ሰዉ ዘንድ ምንም ያልተባለዉና ለግዜዉም ቢሆን ሴራዉ ስላልታወቀበት የዚያን ተራ ወታደር ሚስት ለራሱ አደረጋት::

በተንኮል እንዲሞት የተደረገዉ የኦርዮን ደም ከምድር ወደ ፈጣሪዉ ስለጮኸ ፈጣሪ በንጉሡ ላይ ተቆጥቶ ነዉሩን በአደባባይ ገለፀበት:: እናም እዉነትና ፍትህ በእርሱ የሆኑለት አምላክ ንገሥ ዳዊት በድብቅ በሰራዉ በደል እስከ ሦስት ትዉልዱ ድረስ ዋጋ እንዲከፍልበት አድርጎታል:: ሰዉ የዘራዉን ያንኑ ያጭዳል እንደተባለው በንጉስ ዳዊት ተፈፃሚ ሆኖ አይተናል።

የዘመኔን ትዉልድ እሞግታለሁ ዛሬ ላይ በግልም ሆነ እንደ ማህበረሰብ በአስተሳሰባችንና በምግባራችን ለነጋችን ምን እየዘራን ነዉ? በዘርና በጎጥ እየተቧደንን ለርካሽ ጥቅም በሌሎች ላይ የምንዶልተዉ ደባ ይኖር ይሆን? በመንግስት የኃላፊነት ቦታ ተቀምጠን ግዜን ተገን አድርገንና ስልጣናችን ተመክተን ፍትህን አዛብተን፣ አድሎ ፈፅመን ይሆን? አጋጣሚዉን እየተጠቀምን በማጭበርበርና በሙስና ሃብት ንብረት አከማችተንስ ይሆን? በማለት የዘመኔን ትውልድ ልሞግት ተነስቻለሁ።


ይህ ሁሉ ለግዜዉ የጠቀመን ቢመስልም እንዲያም ሲል በሌሎች ፊት የይምሰል አንቱታ አስገኝቶልን ቢሆን በህግ ተጠያቂ ባያደርገን በየትኛዉም የእዉቀትና የኑሮ ደረጃ ላይ ብንሆንም ህሊናችን አንድ ነገር ያስገነዝበናል።

ያከማቸነዉ ሃብት ንብረት፣ የሰበሰብነዉ ገንዘብ በተኮል ያገኘነዉ በመሆኑ እዉነተኛ እርካታ እደማይሰጠን ያሳየናል። ስለምን? ህሊና ትልቅ ዳኛ ነዉና። እናም ይህ አይነቱ ሁኔታ ዘር ነዉና ወደ ሚቀጥለዉ የዘር ሀረጋችን ማለፉ አይቀሬ ይሆናል። ብዙ ዋጋም ሊያስከፍል ይችላል። እናም ነገን በዛሬ ለማፅናት ኑሮአችንና አካሄዳችንን በመልካም ልንመራ ግድ ይለናል።

ዛሬ ላይ በየማህበራዊ ሚዲያዉ ስማቸዉንና ብሔራቸዉን እየቀያየሩ ሕዝብን ከሕዝብ ብሔርን ከብሔር ጋር በማጋጨት ሀገር ለማፍረስ ቀን ከለሊት የሚተጉት በራካታ መሆናቸውንእያስተዋልን መጥተናል።እነዚህ ኃይሎች እየዘሩት ያለዉ የከፋፋይነት ተግባር የዘሩትን ፍሬ እንደሚያጭዱ የተገነዘቡ አይመስሉም። አንድ ገበሬ ስንዴ ዘር ዘርቶ የገብስ ወይም የማሽላ ምርት ለማግኘት እንደ ማይጥብቀው ሁሉ እነዚህም ወገኖች የፖለቲካ አመለካከታቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ጥላቻንና መለያየትን ሲያራምዱ ዉለዉ እያደሩ ፍቅርና አንድነት የትውልዶቻቸው እጣ ፈንታ እንዲሆን መጠበቅ አይኖርባቸውም:: ማንም የዘራዉን ማጨዱ ተፈጥሮአዊ ህግ ነዉና።

ስለምን ትናንት የሀገሪቱን ስልጣን ሙሉ በሙሉ በዘረኝነት ተቧድነዉ ተቆጣጥረዉ ይህን ምስኪን ሕዝብ በዘርና በሃማኖት ከፋፍለዉ ሲበዘብዙት የነበሩት አካላት ጊዜአቸዉ አልቆ ከነዕኩይ ምግባራቸዉ ታሪክ ወደ መሆን ደረጃ ቢደርሱም በምድራችን የዘሩት ነቀርሳ አስተሳሰብ ነገ ላይ ትዉልዳቸዉን ብዙ መከራ የሚያስከፍል ይመስለኛል።

እናም ትውልዳችን ከዚህ መሰሉ ተጨባጭ ሁኔታ መማር ግድ ይለዋል።ለዚህ ደግሞ የቀናዉን መንገድ ለማሳየት ምሁራኖቻችን ትልቁን ድርሻ ሊወስዱ ይገባል።



## ደቀመዛሙርት

ይህ አምድ በዋነኛነት የተማሪዎች ድምፅ እና ተማሪነትን የሚመለከቱ ፅሁፎች ይቀርብበታል










# ታላቅነት ማለት ምን ማለት ነው? ታላቅ መሆንስ እንዴት ይገለፃል ?

በቢንያም ላቀ

አንድ ሰው ነገሮችን አመዛዝኖ የማወቅ ፍላጎቱ ሲጨምር፣ ማወቅ እና ማድረግ ያለበትን በተገቢው ሰዓት እና ቦታ ሲያከናውን የታላቅነት ስሜት ሊሠማው ይችላል::

ታላቅነት ካለመውደቅ ብቻ ሳይሆን ከውድቀት በመነሳት ጭምር ይረጋገጣል:: ይህም እውቀት ራስን በሚገባ ከማወቅ እንደሚጀምር፣ ብሎም ጠንካራ እና ደካማ ጎናችን በመለየት እንደሚፀና የሚያመላክተን ይሆናል::

በሌላም መልኩ ታላቅነት ከሰዎች በላይ በመሆን ብቻ የሚገለፅ አለመሆኑን ያስገነዝበናል:: ወንዞችን እና ባህሮች ከተራሮች የሚመነጩትን ምንጮች ማስገበር የቻሉት እንደተባለው ከታች በመሆናቸው እንደሆነ ስናስተውል በርግጥም የጉዳዩን ትክክለኛነት መረዳት ይቻለናል::

ወንዞች እና ባህሮች ከተራሮች ስር በመገኘታቸው የትልቅነት መንበራቸውን አላጡም:: እናም አዋቂ ለመባል ሁልጊዜ ከሰዎች በላይ ሆኖ መገኘትን ግድ አይልም::

ትልቁ ነገር ማወቅ የሚገባንን አውቀን ከሌሎች ሰዎች ጋር አብሮ መኖርን መገንዘብና ተግባራዊ ማድረግ ነው:: ከሰዎች ጋር ስንኖር የሰውን ሀሳብ በመጠኑም ቢሆንም ልንጠብቅ ይገባል::

ሰዎች ሃሳባችን እንዲቀበሉን እነሱን ሆነን መቅረብ ግድ ይላል:: እንዲያደርጉልን የምንፈልገውን ነገር ቀድመን ተመሳሳዩን ማድረግ ይጠበቅብናል:: በዚህ አግባብ ከተመራን ደስ ብሏቸው የምንፈልገውን ያደርጉልናል::

"እንዲደረግብህ የማትፈልገውን ነገር በሰዎች ላይ አታድርግ" መባሉ ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው ልብ ይሏል:: ሰዎች እዲያፈቅሩን ከፈለግን መጀመሪያ ፍቅር ልንሰጣቸዉ ይገባል፤ የምንናገረዉን እዲያዳምጡን ቀድመን ሰለራሳቸዉ እንዲነግሩን መፍቀድ ፤እዲያከብሩን ቀድመን ሰዎችን ማክበር ይኖርብናል::

ይህ በኒውተን ሦስተኛ ህግ መሰረት ስናየው እያንዳንዱ ግብረ መልስ እዳለው ሁሉ ሰውችን በገፋናቸው ቁጥር ይገፉናል:: በተቃራኒው ደግሞ በቀረብናቸው ቁጥር እነርሱም ይቀርቡናል::

ሰውች መልካም እንዲሆኑልን መልካም ሆነን ልንቀርባቸው ያስፈልጋል:: ከዚህ ላይ አንድ ጥሩ ምሳሌ ማንሳ ተገቢ ይሆናል::

አሳዎችን ለማጥመድ ወደ ሀይቆች ስንጓዝ እኛ የምንወደውን ክሬም ሳይሆን እነሱ የሚወዱትን ትላትል ከመቃጥናችን ላይ ማስቀመጥ ይጠበቅብናል:: ስለዚህ የሰዎችን ሀሳብ መረዳትና መጠበቅ ከሰዎች ጋር አብሮ ለመኖርንና በቀላሉ ለመላመድ ያስችላል ::

"ውስጣቸውን የሚያዳምጡ ታላቆች ቢሆኑም የሌላን ሰው ውስጥ የሚያዳምጡ እነሱ በርግጥ ይበልጥ ታላቆች ናቸው::" መባሉም ከዚህ መሰረታዊ እውነታ ጋር ጥብቅ ቁርኙት ይኖረዋል::

# ጤንነት

ይህ አምድ የተለያዩ ጤና ነክ ጉዳዮችና ጤንነትን የተመለከቱ ምክረ ሃሳቦች ይቀርብበታል

# የፀረ-ጀርም መድሀኒቶች ተግዳሮት

በዳኝነት ደረበ እና ወንድም መልካም
ህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ

የሰው ልጅ በሽታወች በግርድፉ ከሰው ሰው የሚተላለፉ እና ከሰው ሰው የማይተላለፉ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ከሰው ሰው የሚተላለፉ የሚባሉት በጀርሞች አማካኝነት የሚመጡ ሲሆኑ እንደ HIV/AIDS ፣ ቲቢ ፣ ታይፎይድ ፣ ታይፈስ፣ ጨብጥ ፣ ቂጥኝ ፣ አሜባ ፣ ጃርዲያ ፣ ኮሶ ወዘተ ናቸው። ከሰው ሰው የማይተላለፉ የሚባሉት ደግሞ በአኗኗር ዘያችን ምክንያት የሚመጡ ሲሆኑ እንደ ደምግፊት ፣ ስኳር ፣ የልብ መድከም ፣ ካንሰር ወዘተ ናቸው።

ባሁኑ ጊዜ የአደጉ አገሮች ተላላፊ በሽታወችን ተቋጣጥረዋቸዋል፡ ፡ እንደ ኢትዬጵያ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ግን ሁለቱም አይነት በሽታወች የህብረሰቡ ችግር መሆናቸውን ቀጥለዋል።

እነዚህ ተላላፊ የሆኑ በሽታወችን ለማከም የሚውሉ መድሀኒቶች ፀረ-ጀርም መድሀኒቶች ይባላሉ። በባለፉት ሰባት 10 አመታት ውስጥ ከፍተኛ እድገት ካስመዘገበው የህክምና ዘርፍ ውስጥ ዋናውና አንደኛው የእነዚህ ፀረ-ጀርም መድሀኒቶች እድገት ነው።

ፀረ-ጀርም መድሀኒቶች ገብያ ላይ ከመዋላቸው በፊት ገዳይ የነበሩ ብዙ በሽታወች አሁን ምስጋና ለፀረ-ጀርም መድሀኒቶች በቀላሉ መዳን ይችላሉ። እነዚህ ፀረ-ጀርም መድሀኒቶች በባለፉት ሰባት 10 አመታት ውስጥ የብዙ ሰወችን ህይወት ታድገዋል እንዲሁም ተላላፊ በሽታወችን በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ችለዋል።

ከጥቂት አመታት ወዲህ ግን የተለያዩ በሽታ አምጭ ጀርሞች ለነዚህ ህይወት አድን ፀረ-ጀርም መድሀኒቶች እየተላመዱ ህክምናውን አስቸጋሪ እያደረጉት መጥተዋል። ለምሳሌ ወባ፣ HIV/AIDS፣ ቲቢ ወዘተ ለብዙ ፀረ-ጀርም መድሀኒቶች እየተላመዱ የመጡ በሽታወች ናቸው።

ችግሩን ደግሞ የባሰ እና በጣም አሳሳቢ የሚያደርገው በአሁኑ ጊዜ እምብዛም አዳዲስ የፀረ-ጀርም መድሀኒቶች ወደገቢያ እየገቡ አለመሆኑ ነው። በዚህ ከቀጠለ አንዳንድ በሽታወች ሁሉንም ፀረ-ጀርም መድሀኒቶች ተላምደው ማከም የማንችልበት ጊዜ የመምጣቱ ጉዳይ የማይቀር ይመስላል።

በአሁኑ ጊዜ ፀረ-ጀርም መድሀኒቶች በጀረሞች መለመድ ዋነኛ የማህበረሰብ ችግር ሆኖ በአለም የጤና ድርጅት ከተደነገገ ዋል አደር ብሏል። የአለም የጤና ድርጅት ሪፖርት ሁሉም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ በቅንጅት መስራት ካልተቻለ አንዳንድ ተላላፊ በሽታወች ለሁሉም ፀረ-ጀርም መድሀኒቶች ተላምደ.ው በቀላሉ ገዳይ የሚሆኑበት ጊዜ በጣም ቅርብ ሲሆን እንደሚችል ያስጠነቅቃል።

ይህ እንዳይሆን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ማለትም መንግስት፣ የጤና ባለሙያወች እንዲሁም ማህበረሰቡ ተቀናጅቶ መስራት ይኖርበታል።

የፀረ-ጀርም መድሀኒቶችን መላመድ ምንም እንኳን ተፈጥሯዊ ዑደት አንዱ ምክንያት ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈጠር ይችላል፡ ፡ ከነዚህም ውስጥ ፀረ-ጀርም መድሀኒቶችን ያላግባብ መጠቀም ነው። ሌላው ምክንያት ደግሞ ጥራቱን ያልጠበቀ መድሀኒት ገብያ ላይ ማሰራጨት ነው።

ፀረ-ጀርም መድሀኒቶችን ያለአግባብ መጠቀም

ፀረ-ጀርም መድሀኒቶችን ያላግባብ መጠቀም ስንል ለሰወች ወይም ለእንስሳት ትክክለኛ ያልሆነ ወይም አላስፈላጊ ፀረ-ጀርም መድሀኒቶችን ማዘዝ፣ መጠቀም ማለት ነው። እንደ አለም የጤና ድርጅት ሪፖረት በሀኪም ከሚታዘዙ ፀረ-ጀርም መድሀኒቶች ቢያንስ 50 ከመቶ ያላግባብ ናቸው ። ከነዚህም ውስጥ ግማሾቹ በተጠቃሚወች ዘንድ በአግባቡ ጥቅም ላይ አይውሉም።

ስለዚህ ይህን ያላግባብ ጥቅም ለማሻሻል ከመንግስት፣ ከጤና ባለሙያወች እንዲሁም ከማህበረሰቡ የተለያዩ ሚናወች ይጠበቃል። እንዲሁም ከእንስሳት ሀኪሞች እና ከግብርና ባለሙያወችም ብዙ ይጠበቃል።

በአገራችንም እነዚህ ፀረ-ጀርም መድሀኒቶች ያለአግባብ ጥቅም ላይ እየዋሉ መሆናቸውን የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ ። እንደ ኡመር አብዱ ዳሰሳ ጥናት በአገራችን 49.2 ከመቶ በላይ የሚሆኑት ፀረ-ጀርም መድሀኒቶች የሚታዘዙት ያለአግባብ መሆኑ ይገለፃል። እንዲሁም 43.3 ከመቶ በላይ ተጠቃሚወች ለራሳቸው ፀረ-ጀርም መድሀኒቶችን ያዝዛሉ ።

ተጠቃሚወችም መድሀኒቶችን ከ50 በመቶ በላይ በአግባቡ አይጠቀሙባቸውም። ስለዚህ ይህን ችግር ተባብሮ የመፍታት ስራ የነገ የማይባል ነው።

የፀረ-ጀርም መድሀኒቶች ያለአግባብ ጥቅም ላይ መዋል መንግስት እና የጤና ባለሙያዎች የራሳቸው የሆኑ አሉታዊ ድርሻ ቢኖራቸውም ዋናው ምክንያት ግን ተጠቃሚወች ላይ የሚታዩ የአጠቃቀም ጉድለቶች ናቸው።

ጥራታቸውን ያልጠበቁ ፀረ-ጀርም መድሀኒቶች

ሁለተኛው የፀረ-ጀርም መድሀኒቶች መላመድ ምክንያት ደግሞ ጥራታቸውን ያልጠበቁ መድሀኒቶች ወደ ገብያ መግባታቸው ነው። እንደ አለም አቀፍ የጤና ድርጅት ሪፖረት እስከ 10 ከመቶ የሚደርሱ መድሀኒቶች ጥራታቸውን ያልጠበቁ ናቸው፣ ከነዚህ ውስጥ 50 ከመቶ ፀረ-ጀርም መድሀኒቶች ናቸው፣ እንዲሁም 78 ከመቶ የሚሆኑት ጥራታቸውን ያልጠበቁ የሚገኙት እንደኢትዮጵያ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ላይ ነው።

የችግሩን ስፋት በአገራችን የሚያሳይ የተጠና ጥናት ባይኖርም እኳን ነባራዊ ሁኔታው ከአለምአቀፉ ሁኔታ እንደማይለይ ይታወቃል።

የፀረ-ጀርም መድሀኒቶች መላመድ ለመግታት መደረግ ያለባቸው ተግባራት


የፀረ-ጀርም መድሀኒቶችን መላመድ ችግር ለመቀነስ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተባብሮ ምስራቱ ለነገ የማይባል ስራ ነው።

በዚህም መሰረት ከመንግስትና ከጤና ባለሙያወች ተግባራት እንዳለ ሆኖ ማህበረሰቡ ከዚህ በታች ያሉትን በአግባቡ በመተግበር የፀረ-ጀርም መድሀኒቶች መላመድን ለመግታት ለሚደረገው ጥረት የበኩሉን ድርሻ መጫወት ይገባዋል።

- የግል ንፅህናን በመጠበቅ ተላላፊ በሽታወችን መቀነስ
- ልጆችን ተከታትሎ ማስከተብ
- ፀረ- ጀረም መድሀኒቶችን ከሀኪም ትዛዝ ውጭ አለመጠቀም
- ፀረ- ጀረም መድሀኒቶችን ከመውሰዳችን በፊት የሀኪሙን እና የፋርማሲውን ምክር በትክክል መረዳት
- ፀረ- ጀረም መድሀኒቶችን ሳይቀንሱ ፣ ሳይጨምሩ ፣ሳያቋርጡ እንደ ሀኪሙ እና ፋርማሲው ምክር በትክክል መውሰድ
- ፀረ- ጀረም መድሀኒቶችን ህጋዊ ከሆነ መድሀኒት ቤት ብቻ መግዛት
- መድሀኒቶችን ለሰው አለማጋራት



# ኪነጥበብ እና ባህል




በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ

በባንቹ ታረቀኝ

ዕለቱ አርብ ፣ህዳር አራት ፣2013 ዓ.ም እኔ እና ቤተሰቦቼ ከምሽቱ ሁለት ሰአት አካባቢ ቤት ያፈራውን እራት ቀማምሰን ከጨረስን በኋላ እጃችንን ታጥበን እንደተለመደው ወደ መኝታችን ለመሄድ በመጀመሪያ እናቴ እና ታናሽ እህቴ እኔን ተጋግዘው ከተቀመጥኩበት ወንበር በማንሳት አልጋዬ ላይ አስተኙኝ፤ በመቀጠልም ከእኔ ፊት ለፊት ካለው ሰፋ ያለ የሽቦ አልጋ ላይ ታናሽ እህቴ ተኛች።እናቴ እኛ ከተኛን በኋላ ለእራት የተጠቀምንባቸውን እቃዎች አጣጥባ ቦታ ቦታቸውን ካስያዘች በኋላ የሳልወኑን መብራት አጥፍታ ወደ አልጋ ቤት መጣች፤ወደ ውስጥ እንደገባች ወደ እኔ አልጋ ተጠጋችና ‹‹ደህና እደሪ›› በማለት ዝቅ ብላ ግንባሬን ሳመችኝ፤ከዚያም በሰላም ያዋላትን አምላኳን አመስግና ከታናሽ እህቴ ጋር ተኛች ።

እኔ ባለብኝ ችግር ምክንያት በአንዲት አነስተኛ የጎማ አልጋ ላይ ብቻዬን ነው የምተኛ። ሁላችንም አገር አማን ብለን እንቅልፋችንን በመለጠጥ ላይ እንዳለን ከምሽቱ አምስት ሰአት ገደማ ሰማይና ምድርን ያነጋነገ ተኩስ ተሰማ፣በተኛሁበት ወባ እንዳለበት ሰው መንቀጥቀጥ ጀመርኩ።

እናቴ “ወይኔ ልጆቼ!” በማለት ከአልጋዋ ላይ ተስፈንጥራ በመነሳት ወደ እኔ አልጋ መጣችና ለብሸው የተኛሁትን አሮጌ ብርድልብስ ገልጣ በሀዘኔታ አየችኝ።ታናሽ እህቴ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወስዷታል፤ልጅነት ጥሩ ነው ተሽከመዋት ቢሄዱ እንኳ የምትሰማ አትመስልም።

እየተንቀጠቀጥኩ “ም…ም… ምንድን ነው?” አልኳት።

“ምኑን አወቅሁት ብለሽ ነው ልጄ?” አለችኝ በመርበትበት፤ በመቀጠልም ከአልጋዋ ራስጌ ከተሰቀለው ስዕለ አድኖ ፊት ለፊት በመቆም ሁለት እጆቿን ወደ ሰማይ በመዘርጋት “እመቤቴ፣ ያንድዬ እናት ፣ እባክሽን ይሄን ሌሊት በሰላም እንዲያልፍና ሰው ከሰው እንዲገናኝ ከልጅሽ አማልጅን?” አለች በሚያሳዝን ቅላፄ።

እኔም የእናቴን ሁኔታ ስመለከት ውስጤን ጭንቅ ጭንቅ አለው፤ፍርሃቴ እየጨመረ መጣ። ተኩሱ ቢደገምና ቢያጠፋንስ? ለእኛ ነገ ባይኖር እና ታሪክ ሆነን ብንቀርስ? ምን ላድርግ? አቅም ቢኖረኝ እንደ እናቴ ከስዕለ አድኖው ስር በጉልበቴ ተንበርክኬ ወይም ደግሞ በግንባሬ መሬት ላይ ተደፍቼ እያለቀስኩ ብማጸን እንዴት ደስ ባለኝ፤ ነገር ግን ይሄ ሁሉ ከንቱ ምኞት ነው።

እናቴ ጸሎቷን ስትጨርስ ከእኔ አልጋ ጫፍ ላይ በመቀመጥ አተኩራ ተመለከተችኝ፤ አሳዘነችኝ፣ ስለ እኔ እንደምታስብ ገባኝ። አይበለውና “ከቤታችሁ በፍጥነት ውጡና አካባቢውን ልቀቁ” ቢባል እንዴት እንደምታደርገኝ የምታስብ ይመስለኛል።

“አይዞሽ!” አለችኝ በድንገት።

እኔም አተኩሬ ሳያት የማስበውን ያወቀችብኝ ስለመሰለኝ ትንሽ እንደመርበትበት ብዬ “ከእንግዲህ ምንም ተኩስ አይኖርም አይደል?” በማለት ጠየኳት።ጥያቄዬ እኔንም ሆነ እናቴን ለማሳመን የመሞከር ያህል ነው።

አዘቅዝቃ እያየችኝ “አዎ! ዝም ብለሽ ተኚ” አለችኝ ጭንቅላቴን በቀኝ እጇ ዳበስ፡ ዳበስ በማድረግ።

እናቴ ጡት አለማጥባቷ እንጂ በዚህ እድሜዬ እንደ ህጻን ነው የምትንከባከበኝ፤በመሆኑም በየቀኑ ለእኔ በምትደክመው ነገር አዝናለሁ፣ለውጥ የማይታይበት ድካም፣ ተስፋ ብቻ! ድፍን ሃያ ሦስት አመት ሙሉ ምንም ጠብ ያለ ነገር የለም…

ብቻ ምን አለፋችሁ እናቴ ስትወጣ ስትገባ እኔን ስታየኝ ደስተኛ ለመምሰል ትሞክራለች እንጂ አንድም ቀን እኔ እየሰማሁ አምላኳን ስታማርር ሰምቻት አላውቅም፤ነገር ግን ጓደኞቼ የሚያደርጉትን ማድረግ ፈልጌ ሳልችል ስቀር ታዝናለች።

የእኔ ምስኪን እናት!… በዚህ ምክንያት እርስ በርስ እንተሳሰባለን፣እንዋደዳለን።

እራሴን ታዘብኩት እንዴት ለህይወቴ እንዲህ ልፈራ እና ልሳሳ ቻልኩ? እንዴት ለመኖር ጓጓሁ? ምን ልፈጥር? ለምን ተጨማሪ ጊዜ ፈለግሁ? እስካሁን ለራሴ ምን ሰራሁ? ለቤተሰቦቼ ምን አደረግሁ? ለሀገሬስ ምን የሚጠቅም ነገር አበረከትሁ? ወደ ፊትስ ምን ይፈጠራል? ለምን ለመኖር ተመኘሁ? አላውቅም ብቻ ፈራሁ።

እኒህን ጥያቄዎች ራሴን ስጠይቅ ሌላው ሀሳቤ ደግሞ ማን ያውቃል ነገ አንድ ተአምር ተፈጥሮ ታሪኬ ይቀየር ይሆናል። ቅዱስ መፅሀፍ ላይ ሰላሳ ስምንት አመት ያልጋ ቁራኛ የነበረውን መፃአጉን በአንድ ቃል የፈወሰ ፈጣሪ በእኔም አንድ ቀን ስራውን ይገልፅ ይሆናል በማለት እራሴን አፅናና ጀምር፤እህቴ እንደምትለኝ።

ዓይኔን ጨፍኜ ከሀሳቤ ጋር እሰጥ አገባ ስገጥም እናቴ የተኛሁ ስለመሰላት ከአልጋው ላይ ቀስ ብላ በመነሳት ፊቴን በብርድ ልብሴ ሸፍናኝ ወደ አልጋዋ ሂዳ ተኛች።

ስሜ በእምነት ይባላል፣የሃያ ሦስት ዓመት ወጣት ልበል ወይስ ህጻን? ይህን ታሪኬን አንብባችሁ እናንተ ወስኑት።የምኖረው ከእናቴ እና ከታናሽ እህቴ ጋር በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ11 ነው። አሁን የምንኖርበትን ቤት መንግስት ቦታ መርቶን ከመስራታችን በፊት ቀበሌ አራት አንድ ክፍል ቤት ተከራይተን እንኖር ነበር።ኑሯችን እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ከእጅ ወደ አፍ የሚባል አይነት ነው።

እናቴ እኔን ከመውለዷ በፊት አባቴ በኪራይ ታክሲ እየሰራ በሚያገኙት ገቢ ይተዳደሩ ነበር።አባቴ ሲሰራ ውሎ ሲመጣ እናቴም ከቤት ውስጥ መሰራት ያለባቸውን ነገሮች ስትሰራ ውላ እርሱ ሲመጣ ቡናዋን አቀራርባ ትጠብቀዋለች፤በዚህም ምክንያት በኑሯቸውም ደስተኞች ነበሩ።

ከሁለት አመት የትዳር ቆይታ በኋላ እኔ ተረገዝኩ። አባቴ ለእናቴ የነበረው ፍቅር ቀስ በቀስ እየቀነሰ መጣ፤ በተከታታይ እያመሸ መግባት ጀመረ።እናቴም ለምን እንደሚያመሽ ስትጠይቀው “በጊዜ ቤት መግባት ስለሰለቸኝ ከጓደኞቼ ጋር እየተጫወትኩ ነው” ይላታል፤ይባስ ብሎ አንድ ቀን አድሮ መጣ።

እናቴም በንዴት እርር ድብን ብላ “ምን ሁነህ ነው?” “እኔ አዳጋ ደረሰበት፣ ወይስ አዳጋ አድርሶ ታሰረ ብየ ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ በአይኔ ሳይዞር ሳድር በሰላም ተቀምጠህ ነው የምታስጨንቀኝ? ሁለት ነፍስ ሁኜ አላሳዝንህም? ፈጣሪ የእጅህን ይስጥህ” አለች።አባቴም “ምን ላድርግ ብለሽ ነው?” “ተካበን በድንገት ስላመመው አብሬው ጤና ጣቢያ ሄድኩ፣ከዚያ ማደር አለበት ሲባል አብሬው አደርኩ፣አሁንም መለስ ስላለለት ሀኪሙ መድሀኒት አዝዞለት ወደ ቤትህ ሂድ እንደገና ከተነሳብህ ወረፋ ይዘህ ተመርመር ስላሉት ከቤቱ አድርሼው መምጣቴ ነው” አላት።ተካበ የአባቴ የቅርብ ጓደኛ ነው።

“አንተ ከምታድር ለምን ቤተሰቦቹ አብረውት አያድሩም ነበር?” አለችው እናቴ።

“ከእኔ ጋር አብረን ሻይ ቡና ስንል ነው ሁለት ሰአት አካባቢ በድንገት ውጋት ያጣደፈው፤መሽቶ ስለነበረ ሽማግሌ እናትና አባቱን ከማስደነግጣቸው እኔ ባድር ይሻላል ብዬ ነው” አላት።

‘ ‘ ምንም ሳይነግራቸው ማደሩስ የማያስጨንቃቸው ይመስልሀል፣ልጃቸው እኮ ነው?” አለችው እናቴ።

“ይህንማ አስበን ሀኪሙ ማስታገሻ ሰጥቶት ትንሽ መለስ ሲልለት ለቤተሰቦቹ ስልክ ደውሎ ከጓደኛው ቤት እንደሚያድር እና እንዳይጠብቁት ተናግሯል” አላት አባቴ።

“ዋናው መሻሉ ነው” አለች እናቴ።

አባቴም ጥያቄና መልሱን ከጨረሰ በኋላ ቁርስም ሳይበላ ወጥቶ ሄደ።

ያባቴ ሁኔታ ያጠራጠራት እናቴ ታመመ የተባለውን የአባቴ ጓደኛ ለማግኘት ወደ ቤተሰቦቹ ቤት ስትሄድ መንገድ ላይ ታገኘዋለች፤እንኳንስ ታሞ ሆስፒታል ያደረ ሊመስል ይቅርና…

ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ “ታመሀል ሲባል ሰምቼ ልጠይቅህ ነበር የመጣሁት” ትለዋለች። እንደ መደንገጥ ብሎ “ኸረ የሰይጣን ጆሮ ይደፈን፣ማን ነው እንዲህ ያሟረተብኝ?” አለና “ይኼ ነገር የመረጃ ስህተት እንዳይሆን? ሌላ ሰው ነግረውሽ ሊሆን ይችላል” አላት።

“አይ! እርግጠኛ ነኝ፤ግን

ወደ ገፅ 12 ዞሯል

## ፀሀይ ናፋቂዋ

ከገፅ 11 የቀጠለ

ትናንትና ከንብረት ጋር አብራችሁ አላመሻችሁም?" አለችው፡፡

"ኸረ በፍፁም! ጧት ግን ተገናኝተን ነበር ፤እርሱ ነው እንዴ እንደታመምኩ የነገረሽ?" በማለት ጥያቄዋን በጥያቄ መለሰ፡፡

"አይ ተወው በቃ በደንብ አላዳመጥኩትም ማለት ነው?" በማለት ፊቷን ወደ ቤቷ አዙራ መንገዷን ቀጠለች፡፡ ምንም እንኳ የተጓዘችው መንገድ ሰላሳ ደቂቃ የሚወስድ ቢሆንም በንዴት በመጦፍ አምስት ደቂቃ የፈጀባት ሳይመስላት ቤት ደረሰች፡፡ ቤቷን ከፍታ በመግባት ከቆዳዋ ኩርሲ ላይ በመቀመጥ ማሰብ ጀመረች፡፡ ምን እያከናወነ ነው? ለምን መደባበቅ አስፈለገ? የሚሉ ጥያቄዎች በሀሳቧ መጡ፡፡ የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት አባቴን መከታተል ጀመረች፡፡

ከጥቂት ቀናት በኋላ የፈራችው አልቀረም ከሌላ ሴት ጋር ፍቅር እንደያዘው ደረሰችበት፡፡ስቅስቅ ብላ አለቀሰች፤የመናቅ፣ ያለመፈለግ ስሜት ተሰማት እናም ተናደደች፡፡ በመጨረሻም እንደምንም እራሷን አረጋግታ ወሰነች እርግጠኛውን ከአባቴ ጠይቃ ካመነ ትዳሯን ማፍረስ፣ እርሱ አልፈልግሽም ከማለቱ በፊት መቅደም፣ ለእርሱ ሁለተኛ ሚስት መሆን እንደማትፈልግ መንገር...

አባቴ ከምሽቱ አምስት ሰአት አካባቢ መጣ፤እናቴም ቁጭ ብላ እየጠበቀችው ነበር፣ "ደህና አመሸሽ ውቢት?" አለ ድምፁን ዝቅ አድርጎ፡፡

"ለምን ካመሸህበት አታድርም ነበር? ሁል ጊዜ አንተን እስከ እኩለ ሌሊት ቁጭ ብየ ስጠብቅ ማደር አለብኝ?" አለች በንዴት፡፡አስከሚቀመጥ ድረስ እንኳ ጊዜ ሳትሰጠው፡፡

"እባክሽን ስደክም ነው የዋልኩ አትጨቅጭቂኝ" አለ አባቴ በተሰላቸ ቃል፡፡

"ኸረ¡ ደከምክ?" አለች እናቴ በፌዝ፡፡

"ምን ለማለት ፈልገሽ ነው? ምን ዙሪያ ጥምጥም ትሄጃለሽ? መናገር የፈለግሽውን ለምን በቀጥታ አትናገሪም?" አለ ቆጣ ብሎ፡፡

"አዎ እነግርሀለሁ እስከ መቼ ተደባብቀን እንኖራለን" አለች፡፡

"የምን ድብብቆሽ ነው? ካንች ምን የምደብቀው ነገር አለኝ" አላት፡፡

"ውሸታም ነህ፡ ብዙ ቀን ዋሽተኸኛል፡ እኔም ከዛሬ ነገ ትመለሳለህ ብየ ጠበቅሁህ አንተ ግን እንኳን ልትመለስ ጭራሽ ባሰብህ! ከዚህ በኋላ ግን በቃኝ ስልችት ብሎኛል፡፡" አለች በምሬት፡፡

"ምንድን ነው የዋሸሁሽ? ምን አጉድየብሽ ነው ይህን ያህል የምታማርሪው? ትንሽ ያበዛሽው አልመሰለሽም? እኔ ከጧት እስከ ማታ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳልል እየለፋሁ የማመጣልሽን ቁጭ ብለሽ እየበላሽ ጥጋብ አላስችል አለሽ አይደል?" አለ፡፡

'እውነት! በአንድ ክፍል የኪራይ ቤት እየኖርክ በገነት እንደምታኖረኝ ትናገራለህ አይደል?"

"ጉረኛ አንድ ቢሉህ ታመሻለህ፣ ሲያስፈልግህ ታድራለህ፣ እኔ ቤት ጠባቂህ ነኝ እንዴ? ደግሞስ የማላውቅ ይመስልሀል ሌላ ሴት እንደወደድክ?" አለች በንዴት፡፡

"በቃሽ? ጭንቅላቴ ላይ ልትወጭ እኮ ምንም አልቀረሽ ‹‹‹እፀድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች››› አሉ አበው ሲተርቱ፡፡ከዛሬ ጀምሮ ለምን አመሸህ? ከእነ ማን ጋር ነበርክ? ለምን አደርክ? የሚባል ጥያቄ መስማት አልፈልግም አለበለዚያ ግን..." አለ፡፡

"አለበለዚያ ምን? ጨርሰው እንጂ ለምን ጀምረህ ትተወዋለህ? አይዞህ ተናገር፣ሌላ ወድጃለሁ፣አንች ሰልችተሽኛል፣ በቃሽኝ በለኝ፤ ለነገሩ እኔም ብሆን ከእንግዲህ እንዲህ አይነት ኑሮ በቅቶኛል፡፡" አለች በሚያሳዝን ቅላፄ፡፡

"ሁለት ነፍስ አድርጎ ሰደዳት ልታስብይኝ ነው እንጂ እንዲህ የሚያደርግሽ በጤናሽ አይደለም››አለ የተወሰነ ለስለስ ብሎ፡፡

"እንኳን ሁለት ሦስት ነፍስ ብሆን እንኳ ለአንተ ሁለተኛ ሚስት ሆኜ መኖር አልፈልግም፤ደግሞ ታያለህ እንዴት እራሴን ማስተዳደር እንደምችል" አለች፡፡

"የራስሽ ምርጫ ነው ‹‹‹ጨው ለራስህ ብትል ጣፍጥ አለበለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይወረውሩሀል››› ብለዋል አበው ሲተርቱ"፡፡ አላት

የባሰ አናደዳት ! "እኔ ከአንተ የምፈልገው ያለህን ኮተት ሰብስበህ ነገ በጠዋት ቤቱን ለቀህልኝ እንድትሄድ ነው፤በዚህ ሰአት ቤት ኪራይ ፍለጋ መንከራተት አልፈልግም፣ሽማግሌ ማልፋትም አያስፈልግ የትኛውን ንብረት ሊያካፍሉን? አራት ኩርሲ፣አንድ የሸቦ አልጋ፣ አንድ የእንጨት ጠረጴዛ፣ የእንጀራ ሞሰብ፣የወጥ መስሪያ ድስቶች፣ የውሃ ብርጭቆ፣የሻይ ብርጭቆ፣




የቡና ማፍያ እቃዎች...የፈለግከውን መውሰድ ትችላለህ" አለች፡፡

አባቴ እንደተባለው በጠዋት ተነስቶ ልበሶቹን ብቻ በሻንጣ ይዞ ሾከክ ብሎ ወጣ፡፡እናቴም እርሱ ወጥቶ ሲሄድ ምንም እንኳ ቢከፋት ላለማልቀስ ከራሷ ጋር ታገለች፤እናም እራሷን ለማኖር ምን መስራት እንዳለባት ማውጣት ማውረድ ጀመረች፡ከዚያም አንዲት ጎረቤቷን ስታማክራት ደረቅ እንጀራ እየጋገረች ብትሸጥ የተሻለ እንደሆነ ስለነገረቻት ከቤት ውስጥ ባላት ዱቄት ጀመረች፡፡ገብያውም ቀስ በቀስ እየተለመደላት ሄደ፡፡ከራሷ መተዳደሪያ አልፋ ባንክ መቆጠብ ጀመረች፡፡ይህንን ስራ ፅንሱ ስምንት ወር እስከሚሆነው ድረስ ትሰራ ነበር፡፡

ከአባቴ ጋር ሲፋቱ የሦስት ወር ነፍሰጡረ ነበረች፡፡ሆዷ እየገፋ ሲሄድና የመውለጃዋም ቀን ሲቃረብ ታላቅ እህቷ ከአዴት እንድትመጣ አደረገች፡፡

ምንም ቢሆን ቀን መድረሱ አይቀርምና የእናቴ እርግዝናም ዘጠኝ ወር ሞልቶት በጤና ጣቢያ የዛሬ ሃያ ሦስት ዓመት እኔ ተወለድኩ፤እናቴ እና አክስቴ በጣም ተደሰቱ፤እኔን አክስቴ ታቅፋኝ ወደ ቤት መጡ፡፡ጎረቤት እየመጣ እናቴን "እንኳን ማርያም ማረችሽ?" በማለት ጠየቋት፡፡

የእናቴ ደስታ ብዙ ሳይቆይ ወደ ሀዘን ተቀየረ፤በድንገት ታመምኩ፣ወደ ወለደችበት ጤና ጣቢያ ይዛኝ ሄደች፣የህፃናት ሀኪሙ ተኝቼ እንድታከም አዘዘ፡፡አራሲቱ እናቴ ተኝታ መታረስ ሲገባት ወገቧ እየተንቀጠቀጠ እኔን ማስታመም ጀመረች፡፡

አንድ ቀን ነርሷ የመድሀኒት መስጫ በተደረገልኝ እጄ መድሀኒቱን ስትሰጠኝ እርር ብየ ሳለቅስ እናቴ "ከእንግዲህ ልጄን ከቤቴ ይዤት መሄድ አለብኝ" ትላለች፡፡

"ቢያንስ ሰባት ቀን መቆየት አለብሽ፣ዛሬ አምስት ቀኗ ነው፤ ሁለት ቀን ነው የቀረሽ ታገሽ›› ቢሏት፡ ‹‹ምንም ቢሆን ዛሬ ከዚህ ሆስፒታል አላድርም" አለች፡፡

"ህክምናዋን ሳትጨርስ እወስዳታለሁ ካልሽ መፈረም አለብሽ" ይሏታል፤እርሷም የተባለችውን አድርጋ ይዛኝ ወደቤቷ ሄደች፡፡እንደ እድል ሆኖ ህመሙም ታገሰልኝ፡፡እኔን የምታዝል ትንሽ ልጅ በደመወዝ አስገብታ ክርስትና ካስነሳችኝ በኋላ ስራዋን ጀመረች፡፡

ስድስት ወር እስከሚሞላኝ ድረስ መተኛት እንጂ ሊያስቀምጡኝ ሲሞክሩ አልችልም ነበር፡፡ይሄ ሁኔታየ ያሳሰባት እናቴ ከግል ሀኪም ቤት አዝላ ይዛኝ ሄደች፡፡ ሀኪሙ ሙሉ ምርመራ ካደረገልኝ በኋላ ለእናቴ "አዝናለሁ ወደ ፊት ልጅሽ ቁማ መሄድ አትችልም" አላት፡፡ የጨው ሀውልት ሆና ቀረች፣ያልጠበቀችውን መርዶ ነበር የሰማች፤ቆይታም ወይኔ ልጄ ብላ ስቅስቅ እያለች አለቀሰች፡፡ከዚያ በኋላ ተስፋ ባለመቁረጥ በየፀበሉ እና በየባህል ህክምናው ይዛኝ ዞረች

ወደ ገፅ 3 ዞሯል

# የሳይንስ ጥግ

ይህ አምድ ሳይንስ እና ቴክኖሎጅ ነክ የሆኑ ፅሁፎች ይቀርብበታል

## የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጥበበ ግዮን ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በክልሉ የመጀመሪያ የሆኑ እጅግ ዘመናዊና የተራቀቁ የምርመራ መሳሪያዎችን በቅርብ አስገብቶ ሥራ ያስጀምራል::




ሥራ ከሚጀምሩት መሳሪያዎች መካከል:-

1. 3-Tesla MRI Scanner Machine (Magnetom Spectra, State-of-the-art High Field MRI with the latest technologies)

2. 128 Slice CT Scan Machine (State-of-the-art CT scanner with the latest technologies)

3 . A d v a n c e d 3 D Echocardiography Machine እና

4. Mamography

ይገኙበታል::

እነዚህ የመመርመሪያ መሳሪያዎች በተለይም (3T MRI and 128-Slice CT) በሀገራችን በብዛት የማይገኙ በመሆናቸው የሆስፒታሉን የሕክምና አገልግሎትንና የትምህርት ጥራትን ከማሻሻል ባሻገር የሪፈራል ማዕከል በመሆን የሌሎችን የጤና ተቋማት ችግር ለመፍታትም ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ:: ላለፉት ሁለት ዓመት ሆስፒታሉ እነዚህን መሳሪያዎች እንዲያሟላ ሲጠይቅ ለነበረው ታካሚም ታላቅ እፎይታ ነው::

ከዚህ በተጨማሪ በመጠናቀቅ ላይ ያለው በሀገራችን በግዝፈቱ ሁለተኛ የሆነው የሕክምና ኦክስጅን ማምረቻ ሥራ ሲጀመር ከ550 በላይ የህሙማን አልጋዎች ከማዕከላዊ ማሰራጫ በተዘረጉ ቱቦዎች (ያለ ሲሊንደር ) ወደ ተለያዩ ክፍሎች በቀጥታ ማቅረብ ያስችለዋል:: ለሌሎች ተቋማትም የሕክምና ኦክስጅን በሲሊንደር እየሞላ የማከፋፈል አቅም ስለሚኖረው በባሕር ዳር ከተማና በአካባቢዉ በሚገኙ የጤና ተቋማት የሚታየውን የህክምና ኦክስጅን እጥረት በዘላቂነት ይፈታል::

ድር ቢያብር... እንዲሉ የሕክምና ክፍሎቻችን ዉብና ማራኪ ይሆኑ ዘንድ ማገዝ ለሚፈልጉ ግለሰቦችና ባለሀሃብቶች በራችን ክፍት ነውና መጠው ይጎበኙን ዘንድ ጋበዝን! ከፍ ያለ አስተዋጽዖ ለሚያደርጉ በስማቸው ሆስፒታሉ ዉስጥ ዘላቂ ማስታወሻ እንዲኖር እናደርጋለን::







አዲስ ከገቡት የህክምና መሳሪያዎች በጥቂቱ

## ስብጥር

ይህ አምድ በሌሎች አምዶች ያልተስተናገዱ ልዩ ልዩ ፅሁፎች ይቀርብበታል







የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በጎ/ዙ/ወረዳ ሸሀ ጎመንጌ ቀበሌ እንቦጭ የማስወገድ ዘመቻ

# የእንቦጭ አረምን የማስወገድ ስራው እንደቀጠለ ነው

በወንዳለ ድረስ

የእንቦጭ አረም የሆነ ወቅት በዘመቻ ስራ ብቻ አስወግደን የምንተወው ሳይሆን፤ ሁኔታዎችን በማጤን በዘላቂነት ተከታታይነት ያለው ሀይቁን የመጠበቅ ስራ መስራት ማለትም ውሃውን ከብክለት ሐይቁን በአፈር እና ልዩ ልዩ መንገድ ከመሞላት የመከላከል፤ ከዚህም ባለፈ የማህበረሰብን ተሳትፎ በማጠናከር የሚመለከታቸው ተቋማት በተቀናጀ መልኩ ስራዎች እንዲሰሩ የማድረግ ሃላፊነት እንዳለባቸው እሙን ነው።

በቦታው ሄደን ያገኘናቸው የእንቦጭ አረም አስወጋጅ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዶ/ር ገበየሁ መንገሻ እንደተናገሩት ዩኒቨርሲቲው በጎንደር ዙሪያ የሚገኙ ቀበሌዎች ማለትም ሸሃ ጎመንጌ፣ ምፅርሃ፣ ጎርጎራ ዙሪያ ባሉ ቦታዎች አረሙን ከማስወገድ ጎን ለጎን ቀጣይነት ባለው መንገድ የሀይቁን ደህንነት ለመጠበቅ የተቀናጀ የአካባቢ ጥበቃ ስራ ለመስራት የቁሳ ቁስ ድጋፍና የባላሙያ እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛል። ቀጣይነት ያላቸዉ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ስራወችም በመከናወን ላይ ናቸው።

ይህንንም ለማሳካት ለሰራተኞች ማረፊያና ማደሪያ፣ ለመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ፣ ለጥገና ተግባርና ዕቃ ማስቀመጫ የሚሆን ቤት እየሰራ ይገኛል። ከዚህም ባሻገር የአካባቢውን መሬት መራቆት ለመታደግም እንደ ደንገል፣ ፊላ፣ ረጃጅም እሳሮችና ችብሀ ዛፍ ለመትከል የቦታ ቅድመ ዝግጅት እያመቻቸ ይገኛል ብለዋል።

የቴክኖሎጂ ሽግግር አስተባባሪና የኮሚቴዉ ምክትል ሰብሳቢ የሆኑት አቶ መከተ ሙሉዓለም በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው ከሁለት ዓመት በፊት ከሙላት ኢንጂነሪንግ ጋር በመተባበር ከአራት በላይ ማረሚያ( harvester)፣ ማመላለሻ( transporters)፣ እና ማስተላለፊያ( conveyer) ማሽነሪዎችን ማስገባቱ አውስተው ማሽኑ በሰዓት ከሀይቁ ዳር አረም ይዞ ለመውጣት ባንዴ ወደ ሰባት ደቂቃ ፈጅቶበት በቀን ስድስት ሰዓት ይሰራል።

የዘመቻ ስራው ከተጀመረ ከጥቅምት 9 እስከ ታህሳስ 30 ወደ 27 ሺ ኪዩቢክ በላይ አረም በማሽኑ ብቻ መወገዱን ጠቅሰው የእንቦጭ አረም ለማስወገድ ከዘመቻ ባለፈ የዕለት ከዕለት ድጋፍና ክትትል ያስፈልገዋል ብለዋል።

ባለሙያው አክለውም ቀላል የሚባል ጥገናዎችን ለማድረግ የመለዋወጫ እጥረትን እንደ ተግዳሮት ያነሱ ሲሆን በዩኒቨርሲቲው አመራሮች የተሰጠው ትኩረትና አቅጣጫ ጥሩ መሆኑን እንደ መልካም አጋጣሚ አንስተዋል።

# እንግዳ

ይህ አምድ የዩኒቨርስቲው ሰራተኞች፣ ተማሪዎች ወይም ሌሎች ታዋቂ እና ተፅኖ ፈጣሪ ሰዎች በዕንግድነት ይቀርቡበታል

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲው የፍልስፍና መምህር ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ በአሁኑ ወቅት የማህበረሰብ ሀያሲ፣አንቂ እና ተመራማሪ ሆነው ሀገራቸውን እና ህዝባቸውን በማገልገል ላይ ይገኛሉ:: ሀገራችን ካሏት ምሁራን በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ:: ግልጽ እና ደፋር መሆናቸው ይነገራል:: አንደበተ ርዕቱው ዶ/ር ዳኛቸው ሀገር ወዳድነታቸውም የዘመናትን ድንበር ተሻግሯል::

ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ እጅግ ከተጣበበ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ጊዜያቸውን ሰውተው የናይል ጋዜጣ እንግዳ ሆነዋል::


--መልካም ንባብ:---

ናይል:- በመጀመሪያ ካለህ የተጣበበ ጊዜ ቀንሰህ ለዚህ ቃለ-መጠይቅ ስለፈቀድክልን በጋዜጣው አዘጋጆች እና በባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ ስም እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ:: ዶ/ር እንዲያው በአጠቃላይ ምሁር ስንል ምን ማለታችን ነው? ባህሪያቶቹ እንዴት ይገለፃሉ?

ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ:- 'Well'... ምሁር ማለት የተማረ ማለት ነው:: ችግር ያለው ምሁር ላይ ሳይሆን የተማረ ከሚለው ላይ ነው:: ይህን ማብራራት ያስቸግራል:: ለምሳሌ እኔ የተማረ የሚለውን ብዙ ጊዜ በሁለት ነው የምከፍለው:: በመደበኛ ትምህርት ያለፈ እና በኢመደበኛ ትምህርት ያለፈ:: ሁለቱም ምሁሮች ናቸው:: ምሁር የሚለው ቃል ግን ከዘመናዊነት እሳቤ ጋር አብሮ የመጣ ነው:: እና ምሁር ሲባል ሰውን ለማስተማር በተቋቋሙና በተደራጁ ተቋማት ያለፈ፣ የተወሰነ ሙያ ወይም(Speciality) ይዞ የዘለቀ ማለት ነው ጠቅለል አድርገን ስናየው::

ናይል:- በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ምሁራን ሚናቸውን እንዳይወጡ ሊያደርጓቸው የሚችሉ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው ብለው ያምናሉ?

ዶ/ር ዳኛቸው:- 'Well'... በመጀመሪያ ሚናቸው ምን መሆን አለበት ብለን መለየት አለብን:: በአገራችን ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ያልሸው ምሁር ሚናውን እንዳይወጣ የሚያደርገው ተፅኖ ሌላም ሀገር ጋር ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው:: እዚህ የተለየ ነገር ያለ አይመስለኝም:: እናም.... በ20ኛ ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ ስለ ምሁር ለየት ያለ ነገር የተናገረው አስር ዓመት አመት ታስሮ የሞተው የጣሊያኑ ታጋይ አንቶኒዎ ግራሚሽ ማርክሲስት ፈላስፋ፣ሁለት አይነት ምሁር አለ ይላል:: አንደኛውን "Organic Intelectual" ይለዋል':- ለህዝብ የቆመ፣ ተራማጅ ሀሳብ የሚያፈልቅና የሚያራምድ፣ለነጻነት እና ለፍትህ ተቆርቋሪ መሆኑን ይገልፃል:: ሁለተኛውን ደግሞ (Oppressive Intelectual) ይለዋል:_ ለስርዓት ተገዥ የሆነ፤ አንድን ስርዓት ለማስቀጠል የሚያስፈልገውን ዳኛ፣ አስተማሪ፣ ሳይንቲስት የሚሸፍን በአጠቃላይ ምሁርነቱ ለማህበረሰቡ በጎሳይሆን




ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ የፍልስፍና መምህር እና ተመራማሪ
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ለስርዓቱ ቀጣይነት እንደሆነ ይህ ፈላስፋ ያስገነዝበናል::

በአገራችን ኢትዮጵያም የምናየው ይህንኑ ነው::

እ---ምም.... ሌላው አንድ በቅርቡ እኔ መግቢያውን የፃፍኩለት ዶ/ር አለማየሁ ረዳ "ምሁሩ" የሚል መጽሐፍ ጽፏል:: እሱን እናንተም ካላያችሁ ብታዩት እና በዚህ አጋጣሚም የእናንተን አንባቢዎች መጋበዝ እፈልጋለሁ:: ጥሩ መጽሐፍ ነው የጻፈው:: ከስር ጀምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ዘመናት ብቅ ያሉትን ቄሶችን፣ ሸሆችን፣ ባህላዊ የታሪክ ተመራማሪዎችን አካቶ ፅፏል::

ይህ ምሁር የሚባለው መደብ የሚገርም ነው፤ ለምሳሌ የተማረ እና የነቃ ስለሆነ (Identity) ባርኔጣውን የመለዋወጥ ችሎታው መቻም በጣም ይገርማል:: ትላንት በነበረበት ቦታ አልነበርኩም ይላል:: ፈጽሞ ተለዋዋጭ ይሆናል:: ሲሽከረከር ይታያል ይህ መለዋወጥ ታዲያ በምክንያት እና በሎጅክ አይደለም:: ትላንት "Operessive Intellectual" ሆኖ ሲያገለግል የነበረው በጊዜ በኋላ ደግሞ መበደሉን እረስቶ ጊዜ

ሲያልፍ እንደኔ የተበደለ የተጨቆነ

የለም ይላል:: እራሱን ዞሮ አያይም::

የሚገርም ነው መቸም:: እኔ ግን የበለጠ የማውቀው ስለአስተማሪዎች ነው:: አስተማሪዎች ደግሞ ፀባይ አላቸው::

ያም ሆነ ይህ ምሁሩ በጣም ጠቃሚ ነው(essential Class) ነው:: ምሁሩን ያላቀፈ ስርዓት እንደማይዘልቅ ብዙ ማሳያዎች አሉ:

ናይል:- በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በተቋማት ግንባታ ምሁራን ያላቸው ሚና ምን መሆን አለበት ይላሉ?

ዶ/ር ዳኛቸው:- ያለ ምሁር እኮ ምንም አይነት ተቋም አይገነባም:: ግልጽ እኮ ነው:: ነገር ግን ባገራችን ብዙዎቹ የሞራል ፅናት የላቸውም የሚል ግምት አለኝ:: እኔ ልፈርጃቸው አልፈልግም::

ናይል:- የምሁራን እሴቶችስ የምንላቸው ነገሮችስ አሉ ወይ?

ዶ/ር ዳኛቸው:- አዎ---- ምሁር ለመሆን አለምአቀፋዊ እሴቶች አሉን:: ምንም ጥርጣሬ የለም:: ለምሳሌ: ፍትሀዊነት፣መመርመር፣ሚዛናዊ መሆን፣ አስመስሎ ለጉልበተኛ አለማደር፣ እእ... የተወሰነ (Patiriotism) ሀገር ወዳድ መሆን እና የመሳሰሉት::

ወደ ገፅ 6 ዞሯል



# ስፖርት

ለጤንነት
ለአንድነት
ለፍቅር

ዘወተር፡-
ማክሰኞ
ሀሙስ
ቅዳሜ

በስፖርት አካዳሚ
ሁላችሁም የዩኒቨርስቲው ማ/ሰብ ተጋብዛችኋል



የባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ የታዳጊ ወጣቶች እግር ኳስ ፕሮጀክት

FM 93.3
የጥበብ ድምጽ
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ራዲዮ

